

# የጥቅምት 22/ 1997 የሰማዕታት ቀን 5ኛ አመት መታሰቢያ በቶሮንቶ፤ ካናዳ ተዘከረ

በወያኔ ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ የአግዓዚ ጦርና የደህንነት አባሎች በምርጫ 97 ሳቢያ በሰላማዊ ዜጎችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ጭፍጨፋና እስራት ስደትና መዋከብ የደረሰባቸውን ኢትዮጲያውያንን 5ኛ ዓመት መታሰቢያ ዘንድሮም በቶሮንቶ ካናዳ ተዘክሯል።

ከሁለት መቶ በላይ ኢትዮጵያውያን በግፍና በጭካኔ የተገደሉበት፣ ከ700 በላይ በጥይትና በዱላ የቆሰሉበት፣ ከ40 ሺህ በላይ እስረኞች በየጦር ካምፑና እስር ቤቶች የተጎሩበት፣ በበዙ መቶዎች ደገሞ የተሰደዱበት አሰቃቂ ወቅት በኢትዮጵያውያን የትግል ታሪክ ለዘለዓአለም የሚታወስ ሲሆን ይህንን ወንጀል የፈጸመው የወያኔ እና ግብረ አበሮቹ ለፍርድ ቀርበው ፍትሕ እስኪገኝ ድረስ ትግላችንና ድምጻችን አያቆምም።

በዚህ በኖቬምበር ወር መጀመሪያ በቶሮንቶ ካናዳም የሰማዕታት መታሰቢያ በስበሰባና በህሊና ጸሎት፤ እንዲሁም በአገር ቤት በምርጫ 97 ሰለባ የሆኑት የሟች ቤተሰቦች በተገኙበት በአዲስ አበባ የመኢአድ ቅጥር ግቢ የ5ኛ ዓመት መታሰቢያ ሲዘከርም ሙሉውን ፕሮግራም በስልክ በመከታተልና መልእክት በማሰተላለፍ፤እንዲሁም የቤተሰብ አባላቸውን ለተገደሉባቸው ቤተሰቦች እርዳታ በማሰባሰብና ተቆርቋሪነታቸውን በመግለጽ የዝክረ ሰማዕታትን ቀን በተከታታይ ለአንድ ሳምንት በማሰብ በተጨማሪም የሰማዕታትን ቀን ልዩ ፕሮግራም በፓልቶክ ክፍል በማሰተላለፍ መዘከሩ ታወቋል።

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶና በተለያዩ  የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ኢትዮጳያውያን በጋራ ማክበራቸውና መዘከራቸው የወገኖቻችን ደም የፈሰሰው ለሰላምና ለዲሞክራሲ ለፍትሕና ለነጻነት ሲታገሉ ሲሆን፣ ብዙ መከራና ፍዳውን ያየው ወገናችን መስዋዕትነት የማይረሳና ወደፊትም በቀጣይነት የሚታሰብ መሆኑን ሁሉም አረጋግጧል።

የወገኖቻችን ደም መና ሆኖ አይቀርም!

እጃቸው በደም የታጠበው የወያኔ ዘረኛና አምባገነን መሪዎች ለፍርድ ይቅረቡ!

ኢትዮጵያ በልጆችዋ ትግል ተከብራና ጸንታ ለዘለዓለም ትኖራለች!

